# <u>የታፈነ ሁሉ ይፈነዳል! የተከለከለም ይጣፍጣል</u>!!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

 

<u>*መንደርደሪያ*</u>:

- " Les libertés ne se donnent pas, elles se prennent".  [Kropotkine]
ነፃነት እንደ ስጦታ የሚሰጥ ሳይሆን፤ በትግል በግድ የሚገኝ ነው ::   (ክሮፖትኪን)

- " Je ne suis vraiment libre que lorsque tous les êtres humains qui m'entourent, hommes et femmes, sont également libres "  [Bakounine]
በዙሪያየ ያለ የሰው ልጅ ፍጡር በሙሉ፤ ወንዱም ሴቱም: ነፃ እስካልሆኑ ድረስ፤ ነፃ ሰው አይደለሁም::   (ባኩኒን)

- "Celui qui rêve mais n'agit pas, cultive le cauchemar". [William Blake ]
ዘወትር ከመመኘት በቀር፤ በተግባር የማይተረጉም፤ ቅዠትን ብቻ ያመርታል:: (ዊልያም ብሌክ)

- " Si vous ne pouvez pas voler, alors courez ; Si vous ne pouvez pas courir, alors marchez ; Si vous ne pouvez pas marcher, alors rampez ; Mais quoique vous fassiez, vous devez continuer à avancer."  [Martin Luther King]
በሰማይ መብረር ካልቻላችሁ እሩጡ፤ መሮጥ ካልቻላችሁ ተራመዱ፤ መራመድ ካልቻላችሁ፤ እየዳሃችሁም ቢሆን፤ በመረጣችሁት ዘዴ ወደፊት መጓዛችሁን ቀጥሉ :: (ማርቲን ሉተር ኪንግ)

- " Ne faites jamais rien contre votre conscience même si l'état vous le demande
" ማንም ሰው  ከህሊናው ውጪ፤ መንግሥት እንኳን እንዲፈጽም ቢያዘው፤ በተግባር ማዋል የለበትም "
አልበርት አነስታይን

<u>*መግቢያ*</u> :

የሰው ልጅ የተፈጥሮ ህግጋትን ጠንቅቆ የማወቅ ፍላጎቱ የመበርታቱን ያህል፤ ከጠቃሚዎቹ ጥቅም ሲያገኝ፤ ሊጎዱት ከሚችሉት ደግም የሚያመልጥበትን ዘዴና መፍትሄ በመሻት፤ ሰብዕናው ወይም የዝርያው ሰንሰለት ያለንበት ዘመን ድረስ እንዲደርስ አድርጎታል::
የተፈጥሮ ህግጋትን መረዳትና ማክበር ያልቻሉ ብዙዎች ጠፍተዋል:: አሁንም ይህን ሁለንተናዊ ሕግ መረዳትና ማክበር የማይችሉ ሁሉ፤ በሚፈጥሩት ቅራኔ ከተፈትሮ ሕግ ጋር እየተላተሙ ይጠፋሉ::

ውሃ ሲፈላ ወደ ዕንፋሎት መለወጡ፤ ከዜሮ በታች ሲሆን ወደ በረዶነት መቀየሩ፤ የቀንና የለሊት መፈራረቅ፤ ክብደት ያለው ማንኛውም ቁስ፤ በስበት ሃይል ወደታች በመጎተት መውደቁ፤ የወቅቶች መፈራረቅ፤..........ወዘተ.  ምክንያቱ የተፈጥሮ ሕግጋት ናቸው::

ምሳሌ መጥቀስ ካስፈለገ፤ ባለንበት ዘመን የሰው ልጅ ሃብት ለማግበስበስ ባለው ስግብግብ የአልጠግብ ባይነት ምግባሩ የተነሳ፤ የከባቢ አየርን በተለያዩ መርዛማ ጭሶች በመበከሉ፤ እየደረሰበት ያለው ቅጣት በቂ ምስክር ነው::

ፈጣሪ አዳምና ሄዋንን ፈጥሮ፤ በገነት ያለውን ሁሉ መብላት ትችላላችሁ፤ የዚችን ዛፍ ፍሬ ግን እንዳትበሉ፤ ብሎ ትዕዛዝ ሲሰጥ፤ በዕናታችን ሔዋን አይምሮ ውስጥ ለምን? የሚል ጥያቄ ለመፈጠሩ ድርጊቷ ምስክር ነው:: የፈጣሪ ለአዳምና ለሔዋን፤ በምድረ ገነት ያለውን ሁሉ እንዲበሉ ፈቅዶል፤ የአንዲት ዛፍ ፍሬን እንዳይበሉ መከልከል ጥያቄ አስነሳ:: ለምን ከለከለን? በምን ምክንያት? ከሌሎቹ ተለይታ ትጣፍጥ ይሆን? ኮምጣጣ ናት? ትመራለች? ትፋጃለች? ብንበላትስ? ከሚሉት ጥያቄዎች ጋር፤ ሌሎች ያልደረስንባቸውን ጥያቄዎች አክሎ፤ በእናታችን በሔዋን አይምሮ ውስጥ ጥያቄ አጫረ::

በበኩሌ ለምን? የሚለው ጥያቄ፤ የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ የጠየቀው የመጀመሪያ ጥያቄ፤ ከፈጣሪው ጋር ያጣላው ቢመስልም፤ ጥያቄው ሻል ወዳለ ፍጡርነት አሸጋግሮታል ባይ ነኝ:: አዳምና ሄዋን ከምድረገነት ቢባረሩም፤ ለምን? የሚለው ጥያቄ፤ ማንነታቸውን እንዲያውቁ አድርጓቸዋል::

በተመሳሳይ እነ ኢሳቅ ኒውተን፤ ጋሊሊዮ፤ አነስታይን፤ ግራሃም ቤል፤ ቮልታ፤ ሚካኤል ፋራዳይ.....ወዘተ. ለምን? እንዴት? መቼ? ምን? በምን ምክንያት? ማን? ከማን ጋር? ከምን ጋር?...............ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳትና የተፈጥሮ ሕግጋትን ጠንቅቀው በመረዳት ለሰው ልጅ ጠቃሚ ግኝቶችን አበርክተዋል::

በተፈጥሮ ሕግ ላይ ሰጪና ተቀባይ አይኖርም፤ ሁላችንም ባለመብቶች ነን፤ ሁላችንም በእኩል እንጠቀምበታለን ወይም በጋራ እንጎዳበታለን ::

አየርን ለመተንፈስ፤ ውሃን ለመጠጣት፤ ለማሰብ፤ ለመናገር፤ ያሰብነውን ለመጻፍ፤ አርሶ ለመብላት፤ በነፃነት ለመኖር፤......ወዘተ. የሌሎችን ፈቃድ አንጠይቅም፤ የተፈጥሮ ሕግ ያጎናጸፈን ጸጋዎቻችን ናቸውና::

ወያኔ እነዚህን የተፈጥሮ ሕግጋት በመቃረን፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ፤ አፋኝ ህጎችን በማውጣት ዜጎቹን በመደፍጠጡ፤ ከህዝብ ጋር እየተላተመ ከመሆኑም በላይ፤ ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ በንቅዘት (በሙስና) ተዘፍቆ በስብሷል:: በአገራዊ ብሂል "የዓሣ ግማቱ ከጭንቅላቱ እንጂ፤ አይደለም ከጅራቱ" እንዲሉ::

ይህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ቂም ቋጥሮ ለበቀል ያደባ ቡድን፤ ዛሬም ከ25 ዓመታት የጭቆና አገዛዙ በኋላ የአንድ ጎሳ ነፃ አውጪ ድርጅት እንጂ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የማይወክል በመሆኑና፤ ነፃ አወጣሃለሁ የሚለውን የትግራይ ሕዝብ ጭምር የማይወክል የማፍያዎች ቡድን፤ በአምሳሉ ጠፍጥፎ የፈጠራቸው ሆድ አደሮችን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ውክልና በሌለው ፓርላማ ተብዬ ውስጥ ጎልቶ እየቀለበ፤ ኢትዮጵያን የሚበታትንበት፤ ሕዝቡን የሚዘርፍበት፤ የአገራችንን ድንበር እየቆረሰ የሚሸጥበት፤ የከተማ ነዋሪዎችን የሊዝ ህግ በሚል ከመሬታቸው የሚነቅልበት፤ አርሶ አደሮችን ከመሬታቸው እያፈናቀለ መሬታቸውን የሚቸበችብበት፤ ልጆቻችንን የሚያስርበት፤ ሲያሻው የሚገልበት፤ ኢትዮጵያን በሶስትና አራት ትውልድ በማትወጣው ብድር የሚነክርበት፤ ሕጎችን በማውጣት፤ ወጣቱን በገፍ እንዲሰደድ ያደረገ፤ ሕዝቡን ያስራበ፤ ሰብአዊ መብት በመግፈፍ ዜጎችን ወህኒ ቤት ያጎረ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃነት፤ ዕኩልነትና ፍትህ ነፍጎ፤ የሚያሰቃይ ጨካን አምባ ገነን ቡድን ነው ::

በደርግ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ፤ ከጥቂት ነጋዴዎች (ያውም ከ 10 ከማይበልጡ) በቀር በሚሊዮን የሚቆጠር ሃብት የነበረው ዜጋ አልነበረም:: የአጼ ኃ/ሥላሴ አገዛዝ እንደተወገደ፤ ደርግ የሶሻሊስት ሥርዓት ያወጀበት ዘመን እንደመሆኑ፤ አብዛኛው ዜጋ ገበሬ፤ የመንግሥት ሠራተኛ፤ ጥቂቱ ደግሞ በግል የንግድ ሥራ የተሰማራ እንደመሆኑ፤ የነበረው የኑሮ ደረጃ ልዩነት፤ ከጥቂት ንኡስ ከበርቴዎች በቀር የአንድ መደብ ሥርአት አካል በመሆኑ፤ አብዛኛው ዜጋ ተቀራራቢ ገቢና የኑሮ ደረጃ ነበረው እንጂ፤ እንዲህ እንዳሁኑ፤ ጥቂቶች በዝርፊያ የናጠጡ ሃብታሞች የሆኑበት፤ ብዙሃን ዜጎች ደግሞ በድህነት የሚሰቃዩበት ሥርዓት አልነበረም::

የዛሬ 25 ዓመታት ከደደቢት በረሃ  ቁምጣ ታጥቀው፤ የባረባሶ ጫማ ተጫምተው፤ ጠመንጃ ነክሰው አዲስ አበባ የገቡት፤ በትግራይ ወንድሞቻችንና ዕህቶቻችን ስም የሚነግዱ ወሮ በሎች፤ ልክ የጀርመን ፋሺስቶች በአይሁዳውያን ዝርያዎች ላይ እንዳደረጉት የሃብት ዘረፋ (robbery (spoliation)፤ ወያኔዎችም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ዓይን ያወጣ ዘረፋ፤ (robbery (spoliation) በማድረግ፤ ያለምንም የሥራ ችሎታ፤ ድካምና ጥረት፤ የዕውቀት ደረጃ፤ በአንዲት ጀንበር የአገርና የወገን ሃብት በመዝረፍ፤ ሕዝቡን አደህይተው እነሱ ሚሊየነር እንዲሁም ቢሊየነር ሆነዋል፤ አሁንም እየሆኑ ነው ::

ይህ የ25 ዓመታት የወያኔ ዘረፋ፤ በመንግሥት እጅ የነበሩ የተለያዩ ኢንዱስቲሪዎችን፤ የማምረቻና ማከፋፈያ፤ የትራንስፖርት፤ የእርሻና የንግድ ተቋማትን....ወዘተ. ወደ ግል ሃብትነት( privatization) ማዘዋወር በሚል ሽፍጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ አዎንታ ሳያገኙ እራሳቸው ሻጮች እራሳቸው ገዢዎች በመሆን የሕዝብ አንጡራ ሃብት ዘርፈዋል:: የከተማ መሬትን በተመለከተ፤ አብዛኛውን የከተማ ነዋሪዎች፤ ከነበሩበትና ዕትብታቸው ከተቀበረበት ቤታቸው በማፈናቀል፤ መሬቱን እነሱ ተቀራምተዋል፤ ይህ ድርጊት አሁንም በአዲስ አበባ መሃል ከተማና፤ በከተማዋ አራቱም ማዕዘናት፤ በቡራዩ፤ በኮልፌ፤ በኮተቤ፤ላፍቶ በሃና ማርያም ዙሪያ፤ በሰበታ፤ ....ወዘተ. ተቀነባብሮ ቀጥሏል::

ወያኔ ሆዱ ሰፊ ሲሆን አይምሮው በጣም ጠባብ በመሆኑ አሁንም የመማር ፈቃደኛነቱ ዝቅተኛ ነው። ሃብት ለማጋበስ የተጠናወተውን ልክፍት ለማርካት፤ አዲስ አበባን ማስፋፋት በሚል ሰበብ፤ የኦሮምኛ ተናጋሪ ወንድሞቻችንና አህቶቻችንን መሬት በጠራራ ፀሐይ ሲዘርፍ እጅ ከፍንጅ በሌብነት ተይዞ ጉድ ፈልቶበታል።  የሕዝቡን ተቃውሞ ተቀብሎና አክብሮ፤ እንደመታረም፤ ይባስ ብሎ፤ የመናገር፤ የመጻፍ፤ ሃሳብን በነፃነት የመግልጽና ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብቶችን በማፈን፤ ሃይል መጠቀሙን መርጧ።

**እኛ ደግሞ፤ የታፈነ ሁሉ ይፈነዳል! የተከለከለም ይጣፍጣል !!  መከልከል ክልክል ነው !!**
**የሙቀት መለኪያን በመስበር፤ ሙቀትን መቀነስ አይቻልም !!  እንላለን።**

የሰው ልጅ በተፈጥሮ ሕግጋት ላይ ተመስርቶ፤ ለሰው ልጆች ሰብዓዊ መብቶች መከበር፤ ነፃነት፤ መብትና ክብር ሲል፤ የአስተዳደር ሕግጋትን ያወጣል። ያወጣቸው ሕግጋት ሕዝቡን የሚጎዱ ከሆኑና፤ ሕዝቡ ከተቃወማቸው፤ ወዲያውኑ ሳይዘገይ ባፋጣኝ የወጣው ህግ ተሰርዞ፤ ድርጊቱ መቆም አለበት።

እንኳን ምድራዊ ገዢዎች፤ ፈጣሪም መከልከል ሞክሮ የሰው ልጅ በዕምቢተኝነት የተከለከለችውን ፍሬ በልቶ፤ የማያውቀውን በማወቅ፤ እራሱን ዳግም መፍጠር ችሏል። የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ወንድሞቻችን ትግል፤ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አካል ነው። ከዚህ በፊት አማርኛ ተናጋሪውን ኢትዮጵያዊ ነጥለው በመምታት፤ ሃብቱን በመዝረፍ፤ ከዘር ማጥፋት ያላነሰ ወንጀል ሠርተዋል። ይህ ድርጊት አሁንም እንደቀጠለ ሲሆን፤ ይህ የማነህ ባለተራ ነጥሎ የመምታትና የዘረፋ ዘይቤ፤ የኦሮምኛ ተናጋሪ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ዘንድ ሲደርስ፤ ሌላው ቆሞ በመመልከት ተራውን ይጠብቃል። ለየብቻ እየተነጠሉ በወያኔ በትር ከመመታት፤ በአንድነት ለነፃነት፤ ለፍትህ፤ ለዕኩልነት፤ ለወንድማማችነትና ለጋራ ብልጽግና በመነሳት ከወያኔ የወረራ አገዛዝ አብረን ሁላችንም ነፃ ሕዝብ እንሁን !!

<u>ለኦሮምኛ ተናጋሪ ወንድሞቻችንና ዕህቶቻችን</u> :
ትግሉን የአንድ ጎሳ፤ የናንተ ብቻ ከማድረግ ይልቅ፤ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አካል በማድረግ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ ጋር በአንድላይ አብረን ለዕኩልነት፤ ለአብሮነት፤ ለወንድማማችነት፤ ለነፃነትና ለፍትህ፤ በጥቅሉ ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ማበብ አብረን ብንታገል፤ የድሉ ቀን ይቀርባል።  ከአሁን በኋላ እንደወያኔ ያለ የአንድ ጎሳ፤ ነፃ አውጪ ነኝ የሚል ጠባብ ቡድን፤ ኢትዮጵያን ይገዛል ማለት ዘበት ነው። ሕዝቡ የነጠፈ ፖለቲካና፤ የጎሳ ፖለቲከኞች ቅርሻት፤ ሰልችቶታል። ለየብቻ ትንንሽ ጉልቻዎች ሆነን ወያኔ በላያችን የግፍ ብረድስቱን ጥዶ በዘረኛ አገዛዙ ከሚለበልበን፤ በአብሮነታችን ተቃቅፈን፤ ትልቅና ኩሩ ሕዝብ ሆነን መኖር እንችላለንና የትግሉን አድማስ ለማስፋት ሞክሩ።

<u>ልብ ከሸፈተ ከተማም ጫካ ነው</u> !!
የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ወያኔ ለመሸፈት፤ ደደቢት በረሃ ድረስ መሄድ አያስፈልገውም! መገን ያራዳ ልጅ፤ ልቡ በአምባ ገነኖችና፤ በዘራፊ ወያኔዎች ላይ ከሸፈተ፤ አዲስ አበባም ጫካ ነው !! ደርግም የወደቀው እነሱ እንደሚፎልሉት፤ በነሱ ጦርነት ብቻ ሳይሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ ላይ ልቡ በመሸፈቱ ነበር። እናም ሞያ በልብ !!

<u>በአንድ እጅ ዱላ  በሌላው የሚበላ</u>!
የሰሞኑ "ብሔራዊ ዕርቅ" የሚለው የወያኔ ጫጫታ፤ የተለመደ ማዘናጊያ፤ ወይም ጊዜ መግዣ (በ'ነሱ አባባል ማስተንፈሻ) ሲሆን፤ ወያኔዎች ብዙ ጊዜ የህዝብ ቁጣ ሲያይልባቸው፤ በአንድ ወገን እየተለማመጡ፤ በሌላ በኩል ሲያስሩና ሲገድሉ ቆይተዋል፤ አሁንም የተለመደ የትጥቅ ማስፈቻ ኳኳታ መሆኑን ሕዝቡ ነቄ በመሆኑ ገብቶታል። አንድ ጊዜ እንጂ፤ ሁል ጊዜ የሚታለል እንደሌለ ማን በነገራቸው ?!

<u>ወያኔና ምሑራን፤ "አህያውን ፈርቶ ዳውላውን</u> ! "
ወያኔ የሕዝብ አመጽ እንደ አቡጀዴ ሲወጥረው ጊዜ፤ የሕዝቡን አመጽ ለማስተንፈሻ በሚል የጅል ፈሊጡ፤ ለ 25 ዓመታት ዞር ብሎ ያላያቸውን ምሑራን በራሱ መስፈርት መርጦ ( በራሱ መስፈርት ያልኩበት ምክንያት ወያኔ አዲስ አበባ እግሩ በረገጠ ማግስት ከ 40 በላይ የሚሆኑ የዩኒቨርስቲ መምህራንን በካድሬያዊ መስፈርቱ ብቁ አይደሉም ብሎ ማባረሩን ላስታውሳቸው ብዬ ነው) አሁን ምሑራንን ለግማሽ ቀን ለማወያየት ስብሰባ የመጥራቱን ፌዝ ስንሰማ፤ ወደው አይስቁ ሳቅ ሳቅን።
ለ25 ዓመታት ብቻውን ሲያቦካ የከረመውን የኮመጠጠ ሊጥ፤ በግማሽ ቀን ስብሰባ፤ ምሁራን ወፍራም እንጀራ ጋግረውለት ሊውጥ!!
ምሁራን ሳይፈለጉ፤ እንደ መርገም ጨርቅ የሚጣሉ፤ ጭንቅ ሲበዛ በገመድ የሚጎተቱ ላታም በጎች አይደሉም።
ወያኔ በዚህ የዘቀጠ ድርጊቱ ለምሁራን ያለው ክብርና፤ አመለካከት ምን ያህል አሳፋሪ መሆኑን ያሳያል።
ዛሬም ከ25 ዓመታት በኋላ በዚያች ጠባብ ጭንቅላታቸው ውስጥ አንዲት የዕውቀት ፍሬ ጠብ አላለችም፤ ይገርማል።

- ሃቀኛ ምሑር ለህሊናው ይቆማል እንጂ፤ የአንባ ገነኖችን ቂጣ እየቀላወጠ ለሃጩን አያዝረበርብም !
- ህሊናውን የታደለ ሃቀኛ ምሑር፤ አገሩ ስትሞትና ታሪኳ ሲፋቅ፤ በመቃብሯ ላይ ከበሮ እየደለቀ አይጨፍርም !
- ለህሊናው ያደረ ሃቀኛ ምሑር፤ በሰንካላ ስርዐተ ትምህርት፤ አይምሮ ሰንካላ የሆነ ትውልድ ለአገሩ አያፈራም !
- ህሊናው የሚሞግተው ሃቀኛ ምሑር፤ ሳይማሩ ግብር እየከፈሉ ያስተማሩት የአገሩ ዜጎች፤ ከመኖሪያ ቤታቸውና ከሚያርሱት መሬት ላይ በግፍ ሲፈናቀሉ እያየ እንደ ድመት አያደፍጥም !
- ህሊናው የሚወቅሰው ሃቀኛ ምሑር፤ በግፈኛ ስርዓት ወገኖቹ ሲቀጠቀጡ ዱላ አያቀብልም !
- በመጨረሻ ለህሊናቸው በማደር፤ በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ ሆነው ከተገፋው ወገናቸው ጎን በመቆም፤ ለሙብቱ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በመጮህ፤ ለታሰሩለትና ለተሰደዱለት ምሁራን፤ የህግ ባለሞያዎች፤ ጋዜጠኞች፤ አስተማሪና ተማሪዎች፤ የኪነ ጥበብ ሰዎች፤ ሠራተኛና ገበሬዎች፤....ወዘተ. ያለኝን ክብርና አድናቆት በአክብሮት ልገልጽ እወዳለሁ::

<u>ለአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ አንዲት ምክር፤</u>
- መጥሃፍ ቅዱሱ የሚለው ለሁለት ጌቶች መታዘዝ አትችልም ነውና፤ በአንድ እጅ የማሌሊት ማኒፈስቶ፤ በሌላው መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ የኢትዮጵያን ሕዝብ መግዛት አይቻልምና፤ አንዱን ይምረጡ::
"እኔ ምን አባቴ ላድርግ?" ከማለት፤ ለሕሊናዎ በማደር ከወያኔ አሽከርነት፤ እራስዎን ነፃ በማውጣት፤ ስልጣኑን ለቀው ከህዝብ ጎን ይቁሙ:: የሕዝብን ፍቅር፤ የፈጣሪን ይቅርታ፤ ይቸራሉና፤ ልቦናውን ይስጦት::

<u>ማሳረጊያ</u> :
ለመሆኑ የወያኔ በደል አንገፈገፈን በቃ ለማለት:
. ስንት ሰው ይሙት ?
. ስንት ሰው በእስር ቤት ታስሮ ይሰቃይ ?
. ስንት የሚሆኑ የአገራችን ገበሬዎች ከሚያርሱት መሬት እየተፈናቀሉ መሬታቸው ለድንበር ዘለል ከበርቴ ይቸብቸብ ?
. ምን ያህል የሚሆኑ የከተማ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤቶቻቸውን በወያኔ እየተነጠቁ የጎዳና ተዳዳሪ ይሁኑ ?
. ስንቶቹ ወገኖቻችን በተደጋጋሚ የረሃብ ቸነፈር እየረገፉ የዓለምን ሕዝብ በልመና እናስቸግር ?
. ምን ያህል የሚሆኑ ሴት ልጆቻችን በአረብ አገር የወሲብና የግርድና ሰለባ ይሁኑ ?
. በምን ያህል የሚቆጠሩ ወጣቶች ተስፋ በመቁረጥ አገራቸውን ጥለው ይሰደዱ ?
. ምን ያህል የሚቆጠረውን የኢትዮጵያ ሃብት ወያኔ እየዘረፈ ያዘርፍ ?
. አያትና ቅድም አያቶቻችን በአጥንታቸው ያጠሩት፤ ምን ያህሉ የአገራችን ድንበር እየተቆረሰ ይሸጥ ?
. እንኳን እኛ፤ ሦስትና አራት ትውልድ ሊከፍለው በማይችል: በምን ያህል ዕዳ አገራችን ትዘፈቅ ?
. ለአፍሪካ አገራት፤ የነፃነት ተምሳሌት የነበረ ሕዝብ እንዴት ዛሬ እንደ ባሪያ እየተፈነገለ በወያኔ ይገዛ ?
. ለመሆኑ ብሔራዊ ውርደታችን እስከምን ድረስ ዝቅ ብሎ ሲዋረድ ነው ሕሊናችንን የሚጎፈንነው ?

ጎበዝ እንግዲህ፤
ወያኔ በ25 ዓመታት የወረራ ዘመኑ፤ አብሮነታችንን ቦርቡሮ ጎሰኝነትና ጎጠኝነትን ተክቷል፤ አንድነታችንን አፍርሶ፤ በመሃላችን የዘር ግንብ ገንብቷል፤ አብሮ የመኖር ባህላችንን አጥፍቶ፤ በመሃላችን ጥርጣሬና አለመተማመን ፈጥሯል፤ የነበረውን የወንድማማችነት ፍቅር አጥፍቶ ጥላቻን ዘርቷል፤ ፤ አብሮ ተካፍሎ የመብላት ወጋችንን አፍርሶ፤ ግለኛና ነጣቂ የሆነ የስስት ሥርዓት አስፍኗል፤ መቻቻልና መከባበርን አቀጭጮ፤ንቀትና ትዕቢትን አብቅሏል፤
የአይምሮ ሰንካላ የሚያደርግ ሥርዐተ ትምህርት በመንደፍ አንድ ትውልድ አምክኗል::
የታሪክ ሽፍጥ በመፍጠር፤ በነበረውና ባለው ትውልድ መሃል ስምምነት እንዳይኖር ተንኮል ሸርቧል::
25 ዓመታት ሙሉ ምሑራንን ከአገራቸው ጉዳይ በማግለል፤ ኢትዮጵያ የምሑሁራን ልጆቿ ዓይምሮ ተጠቃሚ እንዳትሆን በማድረግ፤ አገር ገድሏል::

ዛሬ በወያኔ ዘመን፤ በኢትዮጵያ ሠርቶ መኖር የሚያሳፍር፤ ዘርፎ መክበር የሚያስከብር፤ በመሆኑ፤ በህግ አያስጠይቅም:: እናም: ህጋዊ ሌቦች እየዘረፉ ሲከብሩ፤ ንጹሃን ዜጎች እየሠሩ በድህነት ይማቅቃሉ::

ወያኔ በዚህ ሁሉ ድርጊቱ ፤ የጣሊያን ፋሽቶች፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፈጸሙት በላይ የከፋ ወንጀል፤ በገዛ ወንድሞቹና እህቶቹ ላይ ፈጽሟል::
ኤላስ! ኢትዮጵያ ተጣመው ባደጉ በገዛ ልጆቿ የተፈጸመ፤ ትልቅ የታሪክ ጠባሳ ይሏችኋል ይህ ነው !!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !
እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !!

መጋቢት 28 ቀን 2008 ዓ.ም. (06/04/2016)